ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church of Our Savior
4401 Minnehaha Avenue South ♦ Minneapolis, MN 55406
Tel (612) 721-1222


«እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉስ ነው፥ በምድር መካከል መድኃኒትን አደረገ። አንተ ባሕርን በኃይልህ አጸናሃት፤»
መዝ ፸፫፥ ፸፬) ፥ ፲፪-፲፫ Ps. 74: 12-13

ቀን: ነሐሴ 15/2008 ዓ.ም.
ቁጥር: DSMA/0047/2016

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ፤ አሜን!

ሁላችንም እንደምናውቀው እና በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን እንደምንሰማውና እንደምናየው በአሁኑ ጊዜ ቅድስት ሃገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላማዊ ጥያቄ ባቀረቡ ወገኖች እና በንጹሃን ዜጎች ላይ በመንግሥት የጸጥታ ሃይሎች እየተካሄደ ያለው ግድያ፣ እስራት፣ አፈና እና እንግልት ከምንግዜውም የከፋ ደረጃ ላይ ይገኛል።

ቤተክርስቲያናችን ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ዘወትር ለህዝብ እና ለሃገር ከምታቀርበው ጸሎት በተጨማሪ በዚህ ባሳለፍነው የፍልሰታ ሱባኤ ወቅት ስለ ቅድስት ሃገራችን ኢትዮጵያ፣ በአስከፊ የአገዛዝ ቀንበር ሥር ወድቀው ላሉ ወገኖቻችን፣ በግፍ ለተገደሉ፣ በየእስር ቤቱ ለሚንገላቱ፣ በስደት ለሚባዝኑት እና በጭንቅ ውስጥ ላሉት ሁሉ እንዲሁም ስለ እናታችን ቅድስት ቤተክርስቲያን አንድነት ልዩ የጸሎት መርሐግብር ስታደርግ መቆየቷ ይታወቃል።

ባለፉት 25 አመታት በሃገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ በመልከአ ምድር፣ በደም፣ በባሕል፣ በጋብቻ እና በልዩ ልዩ የሕይወት መስተጋብሮች ተሳስሮ የኖረውን ሕዝብ አንድነት ለመለያየት በሃገሪቷ ታሪክ ተደርጎ የማያውቅ ህዝብን እርስ በርስ ወደ መጠፋፋት የሚወስድ በቋንቋ እና በጎሳ ላይ የተመሰረተ የመከፋፈል ፖሊሲ በሥልጣን ላይ ባለው ሥርዓት ሲካሄድ የነበረና አሁንም ህዝብን የመከፋፈሉ ዘመቻ በከፍተኛ ደረጃ እየተካሄደ መሆኑ ከማንም ሊደበቅ የማይችል እውነታ ነው።

ይሁን እንጂ ለረጅም ዘመናት በአንድነት የኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ህዝብን ወደ ማይበርድ የእርስ በእርስ መጠፋፋት ውስጥ ለመክተት እየተደረገ ያለውን ጥረት ባለው የብዙ ሺህ አመታት አብሮ የመኖር ትስስር ያመከነው ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን ችግሩ መልኩን ቀይሮ ከምን ጊዜውም በበለጠ የሃገራችንን አንድነትና ሕልውና እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ አድርሶት ይገኛል።

በዚህም የተነሳ በሃገር ቤት የሚገኘው ወገናችን ትእግስቱ ተማጦ በማለቁ ህዝቡ ራሱን ወደ መከላከል እና በጎጠኝነት ላይ የተመሰረተውን ሥርዓት ለመቀየር ቆርጦ በመነሳት በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ ላይ ይገኛል።

ይህንንም ተከትሎ መንግሥት በሰላማዊ መንገድ ሃሳባቸውን እና ተቃውሟቸውን እያቀረቡ ባሉ በርካታ ንጹሐን ወገኖቻችን ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ በማድረግ በሃገራችን ውስጥ ታሪክ ይቅር የማይለው ግፍና ወንጀል እየፈጸመ ይገኛል።

በመሠረቱ እንዲህ አይነት ጭፍጨፋ፣ ግፍና በደል በህዝብ ላይ ሲፈጸም ከሁሉ አስቀደማ ቤተክርስቲያን ከህዝብ ጐን በመቆም በህዝብ ላይ በደል የሚያደርሰውን አካል በመገሰጽ እና በማውገዝ ህዝቡንም በማጽናናት ቀዳሚ ድርሻ ሊኖራት ይገባ ነበር።

ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት በአገር ቤት ያለችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሥልጣን ላይ ባለው መንግሥት ቁጥጥር ስር በመውደቋ በቤተክርስቲያኗ መንበር ላይ በተቀመጡት አባት ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ በቅርቡ የተሰጠው እና በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የተላለፈው መግለጫ በሃገሪቷ ውስጥ ጥፋት በማድረስ ላይ ከሚገኘው ቡድን መግለጫዎች ብዙም የተለየ ሆኖ አላገኘነውም።

እግዚአብሔር አምላክ በቅዱስ ቃሉ የቤተክርስቲያን አባቶች ዘወትር ከተገፉና ከተጠቁ ጋር እንዲቆሙ፤ ለድሃ አደጎች፣ ለመበለቶች እና ለምስኪኖች እንዲፈርዱ ቢያዝም ዛሬ ግን በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ያሉ አባቶች ከጥቂቶቹ በስተቀር ዝምታን ከመምረጥ ባሻገር ራሳቸውም በግልጽ የዚህ የጥፋት ኃይል ተልእኮ አስፈጻሚ ሆነው ሲሰሩ እና ሲናገሩ እያየናቸው እና እየሰማናቸው ነው።

ጠቢቡ ሶሎሞን በመጽሐፈ ምሳሌ ስለ ቤተክርስቲያን አባቶች እንዲህ በማለት ይናገራል። “አፍህን ስለ ዲዳው ክፈት፥ ተስፋ ስለሌላቸውም ሁሉ ተፋረድ። አፍህን ክፍት፥ በእውነትም ፍረድ፤ ለድህና ለምስኪን ፍረድ።”ምሳ.31 ቁ. 8-9

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለዕብራውያን በላከው መልእክቱ ስለ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ሲናገር "በፈርኦን ቤት ከሚገኘው ገንዘብና ምቾች ይልቅ ከእግዚአብሔር ህዝብ ጋር መከራን መቀበልን መረጠ። "በማለት ከገዳዮች እና ከግፈኞች ጋር ወግኖ ከሚገኝ ጊዜያዊ ጥቅም ይልቅ ግፍንና መከራን ከሚቀበሉ ሰዎች ጐን በመቆም ዘላለማዊ ሕይወትን ማግኘት እጅግ የተሻለ እንደሆነ ያስተምራል።

"ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ፤ ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፤" ዕብራውያን 11፡25-26

ይህም ብቻ አይደለም ። ይህንን የመሳሰሉ በርካታ ታሪኮች በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ተጽፈው ይገኛሉ።

በአንደኛ ነገሥት ምዕራፍ 21 ላይ ተጽፎ የምናገኘው የናቡቴን ታሪክን እዚህ ላይ መጥቀስ እንችላለን። ከዘመዶቹ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መልካም የወይን ፍሬን

የሚሰጥ የጓሮ የእርሻ ቦታ የነበረውን ናቡቴ የተባለውን ሰው የእርሻ መሬት ለመንጠቅ አክአብ እና ኤልዛቤል የሚባሉ ገዢዎች ተባብረው ደሃውን በግፍ በማስገደል መሬቱን ነጥቀውት ነበር። ታላቁ የእግዚአብሔር ነቢይ ኤልያስ ግን ይህንን የንጉሡን እና የንግስቲቷን ግፍ በማወቁ በግፍ ለተገደለው ድሃ በመቆም ገዳዮቹን በግልጽ ተቃውሟል ገስጿል። በኃይላቸው ተመክተው የድሃውን ሰው መሬት በመንጠቅ እና በማስገደል ደሙን ውሾች እንዲልሱት ያደረጉትን አላውያን ነገሥታትም እግዚአብሔር አምላክ በነቢዩ ጸሎት ተበቅሎለታል። 1ኛ.ነገሥት ምዕራፍ 21

ዛሬ በሃገራችን በኢትዮጵያ ይህ አይነቱ ግፍ በስፋት እየተፈጸመ መሆኑን ዘወትር የምንሰማው ጉዳይ ነው። አያሌ ዜጎች ለዘመናት ከኖሩበት ቀያቸው ተፈናቅለው፣ መሬታቸውን ተነጥቀው፣ ከእርሻቸው እና ከቤታቸውን በልዩ ልዩ ምክንያት ተባረው የትም ሜዳ ላይ እንዲቀሩ ተደርጎ ለሞት እና ለብዙ ችግር እየተጋለጡ መሆናቸውን ስናይ በእነ ሙሴ እና በእነ ኤልያስ፣ እንዲሁም በጻድቁ አባታችን ብጹእ አቡነ ጴጥሮስን እና አቡነ ሚካኤል መንበር ላይ ተቀምጠው ያሉት የቤተክርስቲያናችን አባቶች አቋም እጅግ የሚያሳዝን ሆኖ አግኝተነዋል።

ጻዲቁ አቡነ ጴጥሮስ እና ብጹእ አቡነ ሚካኤል ጠላት ሃገራችንን በወረረ ጊዜ የሃገሪቷን እና የህዝቡን አንድነት ለመከፋፈልና ኃይማኖታቸውን ለመበረዝ ለመጣው ጠላት ህዝቡም ሆነ ምድሪቱ እዳይገዙ አውግዘው ታላቅ የአርበኝነት እና የሰማእትነት ተጋድሎ በመፈጸም ለትውልድ መማሪያ የሚሆን ታሪክ ሰርተው አልፈዋል።

አሁን ያሉት አባቶቻችን ግን ይህን የአባቶቻቸውን እና የአባቶቻችንን ታሪክ ዘንግተው ሃገርን እና ህዝብን በጐሳና በነገድ እየከፋፈለ ካለ አስከፊ ሥርዓት ጋር ቆመው በማየታችን በእጅጉ እናዝናለን።

በአሁኑ ሰአት በተለያዩ የሃገራችን ክፍሎች በርካታ ዜጎች በመንግሥት የጅምላ ጭፍጨፋ ህይወታቸውን እያጡ ሲሆን ኢትዮጵያ ሃገሬ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነቴ ያለ ሁሉ ስለ ሃገሩና ስለ ቤተክርስቲያኑ የሚጸልይበት፤ ለሃገር አንድነት እና ለነጻነትም እየተዋደቁ ካሉ ዜጎች ጐን በማንኛውም የድጋፍ ደረጃ የሚቆምበት ወሳኝ የታሪክ ወቅት ላይ እንገኛለን።

ስለሆነም በዚህ የሀገር ህልውና አስከፊ አደጋ ላይ በወደቀበት ወቅት እንዲህ አይነት እልቂት እና ግፍ በወገኖቻችን ላይ ሲፈጸም እያየን በኢትጵያዊነታችንም ሆነ በክርስትና እምነታችን ዝም ብለን የምናይበት ጊዜ ባለመሆኑ ደብራችን ሚኒሶታ ደብረ ሰላም መድኃኒዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከዚህ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ አውጥታለች።

1. በአሁኑ ወቅት በሃገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት መብታቸውን በጠየቁ በንጹሃን ዜጐች ላይ እየተፈጸመ ያለውን ግድያ፣ እስራት፣ አፈና እንዲሁም ከኖሩበት ቀያቸው ዜጐችን ማፈናቀል አጥብቀን በመቃወም መንግሥት ይህን ተግባሩን ባፋጣኝ እንዲያቆም እንጠይቃለን።

2. በሃገሪቱ ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች ሁሉ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ነጻነት፣ ሰብአዊ እና ተፈጥሯዊ መብቶቻቸውን በመጠቀም በሰላማዊ መንገድ ለሚያቀርቧቸው የተለያዩ ጥያቄዎች ከመንግሥት ሰላማዊ መልስ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲመቻች እንጠይቃለን ።

3. ከዓሥሩ የእግዚአብሔር ትዕዛዛት መካከል አትግደል የሚለውን ዘላለማዊ ሕግ ማስተማር ይህንንም ተላልፎ የተገኘን ሁሉ መቃወም ከማንም በላይ የአባቶች ሃላፊነት በመሆኑ፤ በተጨማሪም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእብራውያን መልእክቱ "ከእነርሱ ጋር እንደ ታሰረ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ፥ የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ።" ዕብራውያን 13፡3 በማለት እንዳስተማረው ክርስቲያኖች ባጠቃላይ ይልቁንም ደግሞ በቤተክርስቲያን ሥልጣነ ክህነት ያላቸው አባቶች ሁሉ በመካከላችሁ ያለውን ልዩነት አስወግዳችሁ የንጹሐንን ደም እያፈሰሰ ያለውን ኃይል በማውገዝ እየተገደለ፣ እየታሰረ፣ እየተሰደደ እና እየተገፋ ካለው ህዝብ ጐን በመቆም ሃይማኖታዊ፣ ሃገራዊ እና ታሪካዊ ግዴታችሁን እንድትወጡ በማለት ጥሪያችንን እናቀርባለን።

4. በሥልጣን ላይ ባለው መንግሥት በሃገራችን ውስጥ ህዝብን በጐሳና በቋንቋ በመከፋፈል አንዱን ህዝብ በሌላው ላይ የማነሳሳት እና ወደ ከፋ የደም መፋሰስ የሚወስድ እጅግ አደገኛ አሰራር እና ቅስቀሳ ባስቸኳይ እንዲያቆም እንጠይቃለን።

5. ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን የመናገር የመጻፍና ባጠቃላይ ሃሳባቸውን በነጻ የመግለጽ ተፈጥሯዊ መብታቸውን በመጠቀም የተለየ ሃሳባቸውን በመግለጻቸው ብቻ በየእስር ቤቱ እየተንገላቱ ያሉት በርካታ የህሊና እስረኛ ወገኖቻችን ባስቸኳይ እንዲፈቱ እንጠይቃለን።

6. በሃገራችን ላይ ሥልጣንን ሁሉ በኃይል ጠቅሎ በመያዝ በወገኖቻችን ላይ እጅግ አስከፊ አገዛዝ ያጸናውን መንግሥት በተለያዩ መንገዶች የምትደግፉና የምትረዱ ሁሉ በተለይም የአሜሪካን፣ የእንግሊዝ የቻይና እና የጀርመን መንግሥታት ለዚህ የህዝብን ነጻነትን በመግፈፍ ጭፍጨፋ እያካሔደ ላለው ሥርዓት የምታደርጉትን ድጋፍ እንድትመረምሩ እየጠየቅን ለሰብአዊነት የምታደርጉትን ዕርዳታም በትክክል ለተረጂው አካል ሊደርስ የሚችልበትን መንገድ እንድታመቻቹ እንጠይቃለን።

7. በሃገራችን ውስጥ ዘላቂ ሰላምና አንድነት ተፈጥሮ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በሃገሩ ላይ በሰላም፣ በአንድነት እና በእኩልነት መኖር የሚችልበት ሥርዓት ይመሰረት ዘንድ ሁሉም ዜጋ በነጻነት ተሳታፊ የሚሆንበት እና በብዙሃኑ ህዝብ ተቀባይነት ያለው ህዝባዊ ሥርዓት እንዲመሰረት ለዚህም ባስቸኳይ ብሔራዊ እርቅ እንዲደረግ እንጠይቃለን።

8. በመጨረሻም ቅዱስ ዳዊት በመዝሙር 133 ቁጥር 1 ላይ" ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ፥ እነሆ፥ መልካም ነው፥ እነሆም፥ ያማረ ነው። " በማለት እንደተናገረው በሃገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሃገራት የምንኖር ኢትዮጵያውያን ወገኖች በሙሉ በጎሳ፣ በቋንቋ፣ በአመለካከት....ወዘተ መለያየትን እግዚአብሔር የማይወደው ነገር ብቻ ሳይሆን ሊለያየን ለመጣው ኃይል አውቀንም ሆነ ሳናውቅ የጥፋት መሳሪያ ከመሆን ሌላ ምንም ጥቅም ስለሌለው ጠላት በመካከላችን የዘራውን የመለያየት አሰራር ሁሉ አስወግደን በሃገራችን ላይ በአስከፊ አገዛዝ ምክንያት የተጋረጠውን አደጋ ለመታደግ እንችል ዘንድ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ በአንድነት እንቁም በማለት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ።

ሚኒሶታ ደብረ ሰላም መድኃኒዓለም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ

ግልባጭ፦

- ለአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ጽ/ቤት
- ለተባበሩት መንግስሥታት ድርጅት የጸጥታው ጥበቃ ምክር ቤት
- ለተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብት ድርጅት
- ለአለም አቀፍ የዘር ማጥፋት ወንጀል መከላከል ድርጅት
- ለእንግሊዝ ለጀርመን እና ለቻይና መንግሠታት የውጪ ጉዳይ ጽ/ቤቶች
- በሚኒሶታ የአሜሪካ የህግ መወሰኛው ምክር ቤት ተወካዮች ሚስስ ኤሚ ክሎበሻር እና ሚስተር አለ ፍራንኪን
- ለአሜሪካን ድምጽ የአማርኛ ፣ኦሮምኛ እና ትግሪኛ መርሐግብር ክፍሎች
- ለኢሳት ራዲዮና ቴሌቪዥን
- ለዘሐበሻ ድረ ገጽና ጋዜጣ አዘጋጅ
- በሚኒሶታ ለኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ራዲዮ ዝግጅት ክፍል